በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣ ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር



# ወርሃዊ የአየር ጠባይ ግምገማ እና ትንበያ መጽሔት

## ከኖቬምበር 1-30 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

## እንዲሁም በዲሴምበር 2023

## የሚኖረው የአየር ጠባይ ትንበያ እና ምክረ ሃሳብ

ዲሴምበር 2/2023

አዲስ አበባ

ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል:nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

ርዕስ ገፅ

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ ......................... - 1 -
ምስል 2፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ ........................................ - 3 -
ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ - 3 -
የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........................................ - 3 -
ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት ........................................ - 4 -
የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ ........................................ - 4 -
ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር ........................................ - 4 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........................................ - 5 -
ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ ... - 6 -
እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ ........................................ - 6 -
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ ................. - 7 -
ካርታ 14፡ እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-31፣ 2023 የሚኖረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ .......... - 7 -
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........................................ - 8 -
እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ ........................................ - 9 -



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ ግምገማ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር ወር የበጋዉ ደረቅ፣ፀሃያማ እና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ በተለይም በምስራቅ፣ሰሜን ምስራቅ እና መካከለኛዉ አከባቢዎች ላይ የሚስተዋልበት ወቅት ነዉ፡፡ ይሁን እንጂ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ማለትም የደቡብ፣ ደቡብ ምሥራቅ እና ደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የተሻለ የዝናብ ስርጭት የታየበት ሲሆን፤ በኖቬምበር የሁለተኛዉ አስር ቀናትም በተመሳሰይ ሁኔታ የተስፋፋ የዝናብ ስርጭት የተስተዋለበት ነበር፡፡ በሶስተኛው አስር ቀናት ደግሞ የዝናቡ ስርጭትም ሆነ መጠን  የመቀነስ አዝማሚያ የታየበት እና አብዛኛዉን የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ደረቅ ቀናት የተስተዋለበት ወር ነበር፡፡

በአጠቃላይ በኖቬምበር ወር በደቡብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በደቡብ ምዕራብና በምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ ከባድ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ከባድ ዝናብ ከተመዘገበባቸው ስፍራዎች መካከል በአርባ ምንጭ 32.8፣38.3፤ በሃዋሳ 42.4፤ በጎዴ 30.5፣37.0፤ በነቀምቴ 47.2፣46.2፣31.0፤ በአይራ 48.8፤ በአንገርጉትን 36.2፤ በአርጆ 42.6፤ በበደሌ 41.6፣46.0፤ በቡሬ 32.6፣40.8፣36.6፤ በቡርጂ 39.0፣37.2፤ በቻግኒ 58.5፣57.4፤ በፉኚዶ 46.5፣ 39.6፣ 38.0፤ በጋምቤላ 35.5፣76.6፣38.8፣37.0፣40.0፤ በጋቲራ 30.5፤ በግኒር 40.5፣ 80.0፣ 55.0፣ 34.0 እና 35.5፣ በቡሌሆራ 41.6፣107.4፣ በጃራ 42.9፣ 43.0 እና 34.1 በጂንካ 37.1፣43.4፣ በኮንሶ 63.0፣68.8፤ በላሬ 34.0፤ በልሙገነት 72.0፣ በምዕራብ አባያ 31.0፤ በሞያሌ 31.8፣37.0፣45.0፣56.7፤ በነጆ 57.3፤ በሳዉላ 39.4፣37.6፤ በተርጫ 37.9፤ በመተሃራ 63.5፤ በነገሌ 33.9፤ በአቦምሳ 36.9፣36.0፤ በአልጌ 30.0፤ በአማን 42.7፤ በአሶሳ 35.5፤ በብላቴ 43.5፤ በደምቢ ዶሎ 38.8፤ በዱብቲ 51.0፤ በገለምሶ 35.2፣45.2፤ በሞጣ 47.8፤ በቴፒ 34.2 እንዲሁም በማሻ 80.6 በሚ.ሜ ይገኙበታል።

ባለፈው በኖቬምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም፤በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት ማለትም ከሱማሌ ክልል ጃራ፣ ዶሎ፣ ኖጎብ፣   ቆራሂ፣ ሸበሌ፣ አፍዴር፣ ሊበን እና ዳዋ ዞኖች፤ ከደቡብ ኦሮሚያ ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ እንዲሁም ቦረና ዞኖች፤ ሁሉም የሲዳማ ክልል፤የደቡብ ኢትዮጵያ እና የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ክልል ዞኖች፤ በተጨማሪም ከጋምቤላ ክልል



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et


ኑዌር፣አኙዋክ፣ማዣንግ እና የኢታንግ ልዩ ዞኖች፤ ከቤንሻንጉል ጉሙዝ ክልል አሶሳ፣ ካማሺ እና መተከል ዞኖች፤ እና በምዕራብ ኦሮሚያ ዞኖች ላይ ከ41-300 በሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ9-22 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 9 ና 10) ፡፡ በሌላ በኩል በመካከለኛዉ እና የምስራቅ ኦሮሚያ፣ ምስራቅ መካከለኛዉ እና ምዕራብ አማራ እንዲሁም ሁሉም የትግራይ እና የአፋር ክልል ዞኖች እንዲሁም ድሬዳዋ፣ ሐረሪ እና አዲስ አበባ ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ከ5-41 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ1-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 9 ና 10)፡፡

ባለፈው የኖቬምበር ወር የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር ከአማራ ክልል ሰሜን፣ማዕከላዊና፣ምዕራብ እና ደቡብ ጎንደር፣ ምዕራብ ጎጃም፣አዊ ዞን፣ሰሜን ሸዋ፤ ከአፋር ክልል ዞን 1፤ ሁሉም የሱማሌ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤የሲዳማ፤የጋምቤላ እና የንኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ዞኖች፤ ከኦሮሚያ ክልል ምስራቅ እና ምዕራብ ወለጋ፣ቡኖ በደሌ፣ኢሉባቦር፣ባሌ እና ምስራቅ ባሌ፣አርሲ እና ምዕራብ አርሲ፣ምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ጉጂ እና ምዕራብ ጉጂ፣ ቦረና፣ ምስራቅ እና ምዕራብ ሸዋ፣ ከማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ጉራጌ፣ሀላባ፣ሀዲያ፣ስልጤ፣የየም ልዩ ዞን ከምባታ እና ጠምባሮ ዞኖች እንዲሁም ሀረሪ፣ድሬዳዋ እና በአዲስ አበባ ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 11) ፡፡


በሌላ በኩል የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በምስራቅ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ በአብዛኛዎቹ ቀናት ላይ ከ10 ዲ.ሴ በታች ሆኖ ተመዝግቧል (ምስል 2)፡፡ ከ10 ዲ.ሴ በታች የተመዘገበባቸውን ሥፍራዎች ለመጥቀስም ያህል ፡-



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et





**ምስል 2፡ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ**





ካርታ 9 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 10 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት




ካርታ 11 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## ኢ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በግብርና ሥራ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኖቨምበር የመጀመሪያውና ሁለተኛዉ አስር ቀናት በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት የደቡብ የሀገሪቱ አካባቢዎች በተለይም በሶማሌና በሲዳማ ክልል፣ በደቡብ ኦሮሚያ፣ በደቡብ ኢትዮጵያና በደቡብ ምእራብ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ በመጠንም ሆነ በስርጭት ረገድ የተስፋፋና የተጠናከረ የእርጥበት ሁኔታ ነበራቸው፡፡ የተገኘው እርጥበት በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የተለያዩ ሰብሎች፣ የጓሮ አትክልቶች እና ቋሚ ተክሎች የጎላ ጠቀሜታ ነበረዉ። በተጨማሪም የነበረው እርጥበት ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የተሻለ የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት እንዲኖራቸው ያስቻለ ነበረ:: እንዲሁም በመካከለኛው፣ በምስራቅ፣ ሰሜን ምስራቅ የነበረው እርጥበት ለደረሱና በመሰብሰብ ሂደት ውስጥ በነበሩ ሰብሎች ላይ አሉታዊ ጎን የነበረው ቢሆንም በደጋማ አካባቢ ለሚገኙ እና ሙሉ ለሙሉ እድገታቸውን ላልጨረሱ ሰብሎች፣ ለቋሚ ተክሎች እንዲሁም ከሰብል ስብሰባ በኋላ ለሚዘሩ እንደ ጓያ እና ሽንብራ ለመሳሰሉ የጥራጥሬ ሰብሎች የተገኘው እርጥበት ጠቀሜታ ነበረው። በሌላም በኩል ከነበረው ከፍተኛ እርጥበት ጋር ተያይዞ የዝናብ ውኃን ለመሰብሰብና ለማከማቸት መልካም አጋጣሚን የፈጠረ ነበር፡፡ ነገር ግን በደቡብ ሱማሌና በደቡብ ኦሞ አንዳንድ የሀገሪቱ አካባቢዎች የነበረው ከፍተኛ መጠን ያለው እርጥበት በተወሰኑ አካባቢዎች ላይ የጎርፍ ክስተትና የመሬት መንሸራተት በማስከተሉ በሰው ህይወትና በንብረት ላይ ጉዳት ያደረሰ ነበር፡፡ በአንፃሩም በተወሰኑ የምዕራብ፤ የመካከለኛውና የሰሜኑ አጋማሽ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የነበረው ወቅቱን ያልጠበቀ የእርጥበት ሁኔታ በደረሱ ሰብሎች እና በሰብል ስብሰባ ተግባራት ላይ አሉታዊ ሚና ነበረው። በሌላም በኩል በሶስተኛው አስር ቀናት ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ አመዝኖባቸዉ ተስተዉሏል፡፡ ይህም ሁኔታ ለሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ እንደነበረና በአንፃሩም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የእርጥበቱ መጠንና ስርጭት ቀስ በቀስ የመቀነስ አዝማሚያ የታየበት ቢሆንም ከበጋው ወቅት መግቢያ ጀምሮ በተከታታይ የተስተካከለ እርጥበት እያገኙ ስለነበር የጎላ የእርጥበት እጥረት አልተስተዋለም (ካርታ 12) ።




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et




ካርታ 12 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 የነበረው የአየር ጠባይ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍነው የኖቬምበር ወር በደቡብ ምዕራብ፣ በደቡብ ምስራቅ፣ በደቡብ እና በምዕራባዊ የሀገሪቱ አጋማሽ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት መጠን እንደነበራቸው የተተነተኑ ወራዊ የውሃ ሚቲዎሮልጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ አብዛኛው ገናሌ ዲዋ፣ ኦሞ ጊቤ፣ ባሮ አኮቦ፣ የመካከለኛው እና የታችኛው ስምጥ ሸለቆ ዋቤ ሸበሌእንዲሁም በኦጋዴን ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት ነበራቸው፡፡ በተጨማሪም በጥቂት የላይኛው ተከዜ፣ በታችኛው ዋቤ ሸበላ ፣ እንዲሁም በጥቂት የታችኛው ባሮ አኮቦ ተፋሰሶች ሊይ መጠነኛ እስከ ከፍተኛ እርጥበት የተሰተዋለባቸው ሲሆበኑ በተለይም በተወሰኑ ገናላ ዲዋ እና ዋቤ ሸበላ ላይ በጣም ከፍተኛ እርጥበት አግኝተዋል፡፡ የተቀሩት በአብዛኛው አፍር ዯናክሌ፣ ኦጋዳን ፣ አዋሽ እና ምስራቃዊ ተከዜ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ እና ከፊል ደረቅ ሁኔታ ስር ነበሩ (ካርታ 13)፡፡




ካርታ 13 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 30/2023 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

# እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ

በመደበኛው ሁኔታ በዲሴምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ደረቅ እና ቀዝቃዛ የአየር ጠባይ የሚዘወተርበት ጊዜ ነው። ከዚሁ ጋር በተያያዘ በበርካታ የሀገሪቱ ደጋማ አካባቢዎች ላይ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ የሚያይልበትና አልፎ አልፎ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከዜሮ ዲግሪ ሴልሽየስ በታች የሚወርድበት ጊዜ ነው።

በመጪው የዲሴምበር ወር በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ በዋነኛነት የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ይስተዋልባቸዋል፡፡ ከዚህም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ ሊጠናከር እንደሚችል ይጠበቃል፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በሚኖሩት ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገፅታዎች መጠናከር የተነሳ ከሚኖረዉ የደመና ሽፋን ጋር ተያይዞ በደቡብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ይኖራል፡፡

በአጠቃላይ በመጪው ወር በምዕራብና በደቡብ ኦሮሚያ፤ ከጋምቤላ ክልል የመዠንግ ዞን፤ የደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ፤ የደቡብ ኢትዮጵያ፤የሲዳማ ክልል ዞኖች ላይ ከመደበኛው ጋር የተቀራረበ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በመካከለኛዉ፣ በምስራቅ እና በሰሜን ምዕራብ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ አነስተኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ይኖራል (ካርታ 14)፡፡






ካርታ 14፡ እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1-31፣ 2023 የሚኖረው የዝናብ

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በእርሻ ሥራ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በዲሴምበር ወር በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚኖረው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የእርጥበት ሁኔታ በተለይም የመኸር ሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ ላይ ለሚገኙ አካባቢዎች የዕለት ተግባራቸውን ለማከናወን አመቺ ሁኔታን ይጥራል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮች ይህንኑ መልካም አጋጣሚ በመጠቀም በማሳ ላይ የሚገኙና የደረሱ ሰብሎችን በወቅቱ እንዲያነሱ ይመከራል፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ በአንዳንድ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ እንደሚጠናከርና በተለይም በመስኖ የሚለሙ ሰብሎች፡ አትክልቶችና የፍራፍሬ ተክሎች እና በእንስሳ ጤና ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ሊኖረው ስለሚችል አስፈላጊውን ዝግጅትና ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት በተለይም በደቡብና በደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የሚጠበቀው ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው እርጥበት ጥምር ግብርና ለሚያካሂዱ ለደቡባዊው የሀገሪቱ ክፍሎች በተለያየ እድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ ሰብሎች የውሃ አቅርቦትን ከሚሟላት አንፃር ምቹ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡ በተጨማሪም በአርብቶ አደርና በከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት በጎ ጎን ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም ምዝን የአየር እርጥበት በሚበዛበትና ደመናማ ሆኖ በሚቆይባቸው የመኸር ተጠቃሚ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ለዋግ መፈጠር ምቹ ሁኔታዎች ሊኖሩ ስለሚችሉ አርሶ አደሮች ዘግይተዉ በተዘሩ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ በየጊዜው የማሳ ጉብኝት በማካሄድ ከግብርና ባለሞያዎች ምክረ ሃሳብ በመውሰድ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይመከራል፡፡



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## እ.ኤ.አ ከዲሴምበር 1 እስከ 31/2023 የሚኖረው የአየር ጠባይ አዝማሚያ በውሀው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በዲሴምበር ወር በአብዛኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ ይዘዋተራል፡፡ ስለሆነም በተፋሰሶችና  በግድቦችና የውሃ ኃብት አጠቃቀምን በአግባቡ ጥቅም ላይ ያስፈልጋል። ሆኖም ግን በሰሜን፤ በሰሜን ምዕራብ እና በመካከለኛው የሀገሪቱ ተፋሰሶች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀና ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን የሚደርስ እርጥበት የሚያገኙ ሲሆን፤ በተጨማሪም የበጋ ወቅት ዝናብ ተጠቃሚ በሆኑት በጥቂት የደቡብና የደቡብ ምዕራብ ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እረጥበት ያገኛሉ። ይህም ሁኔታ የውኃ ሃብትን በመጠኑም ቢሆን ከማጎልበት አንጻር አዎንታዊ ሚና የሚኖረው ስለሆነ የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ በማሰባሰብና በማጠራቀም ለሃይል ማመንጫ፣ ለመስኖና ለመጠጥ ውሃ አቅርቦት የተሻለ የውኃ ሀብት እንዲኖር የሚያስችሉ ስራዎችን ማከናወን ያስፈለጋል።



ስልክ +251-11-553-8394 ፋክስ +251-11-552-8713 ኢ.ሜይል፡ nmsa.mafd@ethionet.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et